# አንጋጠው ቢተፉ

ፊሪ እንዳይመስላችሁ!
አንጋጠው ቢተፉ
ተመልሶ ባፉ
ብሎ እሚነግራችሁ
ምሁር ነው መርማሪ
ጠቢብ ጥበበኛ
ግራ ያልተጋባ
እንዳሁን እንደኛ::

ደረጀ መኩሪያ

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

## ምድር ሰትታማ

አቤት የች ምድር ይች የኛ ፕላኔት
በዚህ ሰሞን ደግሞ ከቀድሞ ባሰባት
የኛ የሰው ስስት አልጠግብ ባይነት
ወደላይ ንሮባት! ሚዛኗን አሳጣት!
እያሉ ሲያወጉ ሰምታ ይህን አሜት
መች ደከመኝ አለች ምደር አፍ አውጥታ
ገና ሳይነካ በጉያዬ ያለው የውስጤ ይዞታ
በዙሪያዬ ከቦኝ አየር አፅዋቱ
ይኖራል በውስጤ በቅጥ በስራቱ

የታመቀው ውስጤ ያለኝ ሃብት በሙሉ
መች ተዝቆ ያልቃል ሰዎች ባይባሉ
የተፈጥሮ ህግን እያመሳቀሉ

ባንድ ወገኔ በኩል በሳት ለበለቡኝ
በኬሚካል አረር በኒኩሌር አጋዩኝ
በጭስ ኢንዱስትሪ ዙሪያዬን ከበቡኝ
ባውቶሞቢል ነዳጅ በሰማይ በረራ
በጠዋት ለሰው ልጆች አየር የተጣራ
እንዳልሰጥ አድርገው በራሳቸው ስራ
ምድር አለቀባት ሆናለች ቃጠሎ
የፀሃይ ግርዶሿም ካናቷ ተነድሎ
በዋልታዋ ያለው በረዶዋ ቀልጦ
የአየር ንብረቷና ወቅቷ ተለዋውጦ
ልጆቿን መመግብ ለማኖር በቅጡ
ተስኗታል ብለው ወሬ ሲያጣፍጡ
በሰሞኑ ዜና በኔው ተደመጡ

አሁንም መልክቴ ላዳም ዘር በሙላ
አለኝ የምነግርህ መልካም አዲስ መላ
ወሬና ወቀሳ ምን ይረባል ለኔ
አንድ ዛፍ ይሻላል ሻጥ አርግ ከጎኔ!
የያዘኝ ትኩሳት እንዲቀንስለኝ
አናት ምድር አያልክ ችግኞች አፍላብኝ
ዛፎች ትካልብኝ
አረንጓዴ አልብሰኝ
መልሼ ልክስህ ሙሉ ጉልበት አለኝ
ደረጀ መኩሪያ

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

***Back to Meskot***

***The views reflected in the above poem are solely of the author and are not necessarily shared by*** *Meskot****. You may contact Dereje Mekonen for comments at*** drj_mekonen@yahoo.co.uk**.**